**ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች**

(አርብ—የምሽት ክፍለ ጊዜ)

መልእክት ሦስት

**ቤተ ክርስቲያን በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ መሆኗ፣**
**አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የክርስቶስ አካል መገለጦች መሆናቸው**
**እና አማኞች የቤተ ክርስቲያን ሕይወትን በአካሉ ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ**
**በተግባር መለማመዳቸው**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ተሰ. 1፡1፤ 2 ተሰ. 1፡1፤ ማቴ. 16፡18፤ 18፡17፤ 1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡12-27

**I. ቤተ ክርስቲያን በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ናት—"በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን"—1 ተሰ. 1፡1፡-**

ሀ. በ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡1 ቤተ ክርስቲያን ልዩና ብቸኛ በሆነው አምላክ ውስጥ የመሆኗ እና ይህም አምላክ አባታችን እና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመሆኑ እጅግ አስገራሚ ሃቅ መገለጥ አለን፡-

1. ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ብቻ አይደለችም፤ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ውስጥና በክርስቶስ ውስጥም ጭምር ነች።
2. በአጥቢያችን ያለችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ውስጥ፣ የክርስቶስና በክርስቶስ ውስጥ መሆኗን ማየታችን አስፈላጊ ነው።

ለ. ቤተ ክርስቲያን ከሰዎች የተዋቀረች ናት፣ ነገር ግን፣ እነርሱ፣ አማኞች፣ በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ናቸው—ቁ. 1; 2 ተሰ. 1፡1።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን በሕይወቱና በባሕሪው ከእግዚአብሔር አብ የተወለዱ እና ከክርስቶስ ጋር ወዳለ ሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ የመጡ የሰዎች ቡድን ናት፡-

1. ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ውስጥ እንድትሆን፣ እግዚአብሔር አባታችን መሆን አለበት፣ እኛም ከእርሱ ጋር በሕይወት የሆነ ግንኙነት ያለን መሆን አለብን—1 ዮሐ. 3፡1፡-
   ሀ. በ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡1 *አብ* የሚለው ቃል በሕይወት የሆነን ግንኙነት ያመለክታል፤ በእግዚአብሔር አብ፣ በድጋሚ ተወልደናል፣ ዳግም ተወልደናል፣ አሁን እንደ ልጆቹ ከእርሱ ጋር የሕይወት ግንኙነት አለን—ዮሐ. 1፡12-13።
   ለ. ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር አብ ውስጥ መሆኗ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዓላማ፣ እቅድ፣ ምርጫና አስቀድሞ መወሰን ውስጥ መኖሯን ያመለክታል—ኤፌ.1፡4-5።
   ሐ. በእግዚአብሔር አብ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ልዩና-ብቸኛ ጀማሪና አመንጪ በሆነው በእርሱ ውስጥ ያለች ቤተ ክርስቲያን ናት—ሮሜ 11፡36፤ 1 ቆሮ. 8፡6፤ ማቴ. 15፡13።
2. በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ መሆን እርሱ በሆነውና ባደረገው ሁሉ ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ነው—1 ተሰ. 1፡1፤ 1 ቆሮ. 1፡30፡-
   ሀ. በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ከአሮጌው ፍጥረት የሆነ ነገር ሁሉ መወገድ አለን፣ ምክንያቱም በክርስቶስ ውስጥ መሆን አሉታዊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ በሚያስወግደው በእርሱ ሞት ውስጥ መሆን ነው—ሮሜ 6፡4።
   ለ. በ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡1 *ክርስቶስ* የሚለው ስያሜ የትንሣኤ ብልጥግናዎችን ሁሉ ያመለክታል፤ በመሆኑም በክርስቶስ ውስጥ መሆን በትንሣኤ ውስጥ መሆን ነው—ሮሜ 8፡10-11።

መ. ቤተ ክርስቲያን በሂደት ባለፈው ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ናት—አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ—እርሱም ከአብና ወልድ ጋር ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ የሆነው ነው—1 ቆሮ. 15፡45፤ ዮሐ. 14፡17፣ 23።

**II. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሆነ አጥቢያ ውስጥ ያለች የክርስቶስ አካል መገለጥ ናት—1 ቆሮ. 1፡2፤ 10፡32፣ 17፤ 12፡12-13፣ 20፣ 27፡-**

ሀ. ልዩና-ብቸኛዋ የክርስቶስ አካል በሦስታንዱ አምላክ ዘንድ እንዳለው በመለኮታዊው አንድነት ውስጥ እና በመለኮታዊው ባሕሪ፣ ንጥረ-ነገር፣ ውስጠ-ነገር፣ መገለጥ፣ አገልግሎትና ምስክርነት በብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ትገለጣለች፤ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም አንድ አካል ስለሆኑ አንድ መለኮታዊ ባሕሪይ፣ አንድ መለኮታዊ ንጥረ-ነገር፣ አንድ መለኮታዊ ውስጠ-ነገር፣ አንድ መለኮታዊ መገለጥ፣ አንድ መለኮታዊ አገልግሎትና አንድ መለኮታዊ ምስክርነት አላቸው—ራእ. 1፡11፤ ዮሐ. 17፡11፣ 21፣ 23።

ለ. በማቴዎስ 16፡18 የተገለጠችው ቤተ ክርስቲያን ልዩና-ብቸኛዋ የክርስቶስ አካል፣ አጽናፍ-ዓለማዊዋ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፣ በ 18፡17 የተገለጠችው ቤተ ክርስቲያን ግን በሆነ አጥቢያ ውስጥ ልዩና-ብቸኛ የሆነችው የክርስቶስ አካል መገለጥ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ናት።

ሐ. አንዷ አጽናፍ-ዓለማዊዋ ቤተ ክርስቲያን—የክርስቶስ አካል—ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት—የክርስቶስ አካል አጥቢያዊ መገለጦች—ትሆናለች—ሮሜ 12፡4-5፤ 16፡16።

መ. ልዩና-ብቸኛዋ የክርስቶስ አካል እንደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በብዙ አጥቢያዎች ትገለጣለች—ኤፌ. 4፡4፤ ራእ. 1፡4፣ 11፡-

1. የክርስቶስ አካል የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ምንጭ ነው—ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡21-22።
2. አጽናፍ-ዓለማዊው አካል ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደ አባት ነው፣ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ደግሞ ለአባትየው እንደ ልጆች ናቸው—ሮሜ 12፡4-5፤ 16፡4።

ሠ. እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የልዩና ብቸኛው፣ የአጽናፍ-ዓለማዊው የክርስቶስ አካል ክፍል፣ የዚህ አካል አጥቢያዊ መገለጥ ናት—ኤፌ. 4፡4፤ 1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡27፡-

1. አጽናፍ-ዓለማዊ በሆነ መልኩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንድ አካል ናቸው፣ አጥቢያዊ በሆነ መልኩ ደግሞ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአጽናፍ-ዓለማዊው አካል አጥቢያዊ መገለጥ ነው፤ ስለዚህ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካሉ ሳትሆን የአካሉ ክፍል፣ የአካሉ መገለጥ ብቻ ናት።
2. አጽናፍ-ዓለማዊው ክርስቶስ በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የራሱ ክፍል አለው፤ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ክፍል ነው፣ እነዚህ ሁሉ ክፍሎችም አካሉን ያዋቅራሉ—ኤፌ. 1፡23፤ 2፡22።

ረ. የቤተ ክርስቲያን አጥቢያዊ መቆሚያ ስፍራ መሠረታዊ በሆነ መልኩ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሚተገበር የክርስቶስ አካል ልዩና-ብቸኛ አንድነት ነው—4፡4፤ 1 ተሰ. 1፡1፡-

1. አጽናፍ-ዓለማዊው የክርስቶስ አካል እና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ልዩና-ብቸኛ በሆነ መልኩ አንድ ናቸው።
2. በአጽናፍ-ዓለም ሁሉ አንድ ልዩና-ብቸኛ አካል አለ፣ በእያንዳንዱም አጥቢያ አንድ ልዩና-ብቸኛ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አለ።
3. ይህ ልዩና-ብቸኛ አንድነት በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መሠረታዊው ንጥረ-ነገር ነው—ሐዋ. 1፡14፤ 2፡46፤ 1 ቆሮ. 1፡10፤ ፊልጵ. 1፡27፤ 2፡1-2።

ሰ. በተለያዩ አጥቢያ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ለክርስቶስ አጽናፍ-ዓለማዊ መገለጥ ናቸው—ኤፌ. 1፡23፤ ራእ. 1፡4፣ 11፤ 22፡16፡-

1. ሁሉንም ነገር አጥቢያዊ የሚያደርግና አጥቢያውን ብቻ የሚገልጥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተነጠለ አጥቢያዊ ቡድን፣ አጥቢያዊ ክፍፍል ሆኗል።
2. ለአካሉ የሆኑ መሠረታዊዎቹ ነገሮች ሁሉ አጥቢያዊ አይደሉም—መንፈስ፣ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የሐዋርያት ትምህርት እና የሐዋርያትም ኅብረት።

ሸ. በሃሳባችን አካሉ መቅደም አለበት፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ መከተል አለባቸው—ማቴ. 16፡18፤ 18፡17፤ ኤፌ. 4፡4፣ 16፤ 2፡21-22፤ 1 ቆሮ. 12፡12፤ 1፡2፡-

1. አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር የኢኮኖሚው ግብ—የክርስቶስ አካል—ላይ ለመድረስ የሚወስዳቸው የክንውን ሂደቶች ናቸው—ሮሜ 16፡1፣ 4፣ 16፤ 12፡4-5።
2. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችንን እንደ የክርስቶስ አካል ክፍል ማሰብ ይገባናል—1 ቆሮ. 1፡2፤ 10፡16-17፤ 12፡12-13፣ 20፣ 27።

## III. የቤተ ክርስቲያን ሕይወትን በተግባር በመለማመዳችን ውስጥ የአካሉ ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ ሊኖረን ያስፈልጋል—ቁ. 12-27፡-

ሀ. የአካሉ ሕይወት እንዲኖረን፣ የአካሉን ራስ ስሜት እንደ የራሳችን ስሜት በመውሰድ ለአካሉ በስሜት የተሞላን መሆን አለብን—ሮሜ 12፡15፤ 1 ቆሮ. 12፡26-27፤ ሐዋ. 9፡4-5፡-

1. እንደ ብልቶች በሁሉም ነገር የአካሉ ራስ ስሜት ካለን እና ለአካሉ ግድ ከተሰኘን፣ አካሉን በአእምሯችን፣ በአስተሳሰባችን፣ በቃሎቻችን እና በድርጊቶቻችን ውስጥ እንዳለ ገዢው ሕግ እንወስደዋለን—ኤፌ. 4፡15-16፤ ቆላ. 2፡19።

2. ራሳችንን መካድ እና ራሳችንን ከአካሉ ጋር አንድ ማድረግ አለብን (ማቴ. 16፥24፤ ሮሜ 12፥4-5፣ 15፤ 1 ቆሮ. 1፥2፤ 12፥12-27)፤ ይህን ካደረግን የምንኖረው ሕይወት የአካሉን ሕይወት ይሆናል፣ ጌታም የአካሉን መገለጥ ያገኛል—ኤፌ. 4፥15-16፤ 1፥22-23።
3. የክርስቶስ ድሰታችን የክርስቶስ አካል ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ ያለን እንድንሆን ያደርገናል—ቆላ. 2፥16-17፣ 19።

ለ. የምናደርገው ነገር ሁሉ አካሉን ይመለከታል፤ ስለዚህ፣ የሆነ ነገር በምናደርግ ጊዜ ሁሉ፣ ተገቢ የሆነ የአካሉ እሳቤ ሊኖረን ይገባል—2 ቆሮ. 8፥21፤ ኤፌ. 4፥16፦

1. ለአካሉ ግድ ባለመሰኘት ማንኛውንም ነገር ማድረግ የለብንም—1 ቆሮ. 12፥12-27።
2. ስለምናደርገው ነገር አካሉ እንዴት ሊሰማው እንደሚችል እና አካሉ፣ ምለሳው፣ እንዴት ምላሽ ሊሰጥ እንደሚችል በጥንቃቄ ማሰብ ያስፈልገናል።
3. የምንመላለስበት መንገድ አካሉን በማየታችን ልክ ላይ ይመረኮዛል።
4. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ብቻ በአንድ ልብ ከሆንን እና ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ግድ የማንሰኝ ከሆነ፣ እንደዚህ አይነቱ በአንድ ልብ መሆን የተነጠለ ቡድን፣ ክፍፍል ነው—ሐዋ. 1፥14፤ 15፥25።
5. አካሉን የምንንከባከብ እና ለአካሉ ግድ የምንሰኝ ከሆንን፣ ችግሮች አይኖሩም—ኤፌ. 4፥4፣ 16።

ሐ. አንዱን አጽናፍ-ዓለማዊውን የክርስቶስ አካል በሚያዋቅሩት በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መካከል፣ የክርስቶስ አካል ኅብረት እንጂ ድርጅት የለም—ሐዋ. 2፥42፤ 1 ዮሐ. 1፥3፤ 1 ቆሮ. 1፥9፤ 10፥16-17፤ 11፥29፦

1. በምድር ላይ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንድ አካል ናቸው፣ በዚህም አንድ አካል ውስጥ የመለኮታዊው ሕይወት ዝውውር—የአካሉ ኅብረት—አለ—1 ዮሐ. 1፥3።
2. ኅብረት ከአንድነት ጋር የተገናኘ ነው፤ በአካሉ ውስጥ ያለው የመለኮታዊው ሕይወት ዝውውር የአካሉን ብልቶች ሁሉ ወደ አንድነት ውስጥ ያመጣቸዋል—ኤፌ. 4፥3-4፤ ሮሜ 16፥1-23።
3. የክርስቶስን አካል አጽናፍ-ዓለማዊ ኅብረት ለመጠበቅ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በምድር ላይ ካሉ እውነተኛ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጋር ኅብረት ማድረግ አለባቸው።
4. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አጥቢያዊ ቢሆንም (ሐዋ.14፥23)፣ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት አጽናፍ-ዓለማዊ ነው (2፥42)፤ በብዙ ከተሞች አብያተ ክርስቲያናት አሉ፤ ነገር ግን በመላው አጽናፍ-ዓለም አንድ ኅብረት አለ።

*© 2021 Living Stream Ministry*